# የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
# UNITED ETHIOPIAN DEMOCRATIC FORCES (UEDF)

ቀን፡- ግንቦት ፲፪ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ/ም
Date: ____________________
ቁጥር፡- ኢዴኃኅ/017/98
Ser.No.:____________________

ከኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
በዩትሬክት ከተማ ሆላንድ የተቃዋሚ ኃይሎች ስብሰባ ተሳታፊዎች
ባሉበት

**<u>ጉዳዩ፡- ስለ ስብሰባው ያለንን አቋም ስለማሳወቅ፤</u>**

የአገራችንን ውስብስብ ሁኔታ ለመፍታት የፖለቲካ ድርጅቶች መሰባሰብ አስፈላጊ መሆኑን ከማንም በላይ ኢዴኃኅ ያሰበበትና ተግባራዊ እንቅስቃሴ ያደረገበት ዓቢይ ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም የፖለቲካ ድርጅቶች በቅርብ እየተመካከሩ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየከፋ የመጣውን የአገራችንን የቀውስ ሁኔታ ለመቋቋም ብቻ ሳይሆን የሕዝባችንንና የአገራችንን የወደፊት የጋራ ዕድል ዘለቄታዊነት ባለው መንገድ በጋራ ለመፍታት የሁላችንም ኃላፊነት ስለሆነ የጋራ ተግባራዊ እንቅስቃሴ እንዲደረግ በተለይ ለቅንጅትና ለኦነግ ጥር ፲፯ ቀን ፺፰ ዓ/ም ደብዳቤ መጻፋችን ይታወሳል፡፡ ኦነግም የካቲት ፳፯ ቀን ፺፰ ዓ/ም በሰጠን የጽሑፍ አዎንታዊ ምላሽ መሠረት ሃሳባችን ተግባራዊ ስለሚሆንበት ተከታታይ ውይይቶችን ማድረጋችን ይታወቃል፡፡

ለግንቦት ፲፩ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ/ም (ሜይ 19፣ 2006) በሆላንድ አገር ዩትሬክት ከተማ በኦነግ የተጠራው ስብሰባ ላይ እንድንገኝ ስብሰባውን ከጠራው ድርጅት ከኦነግ ግንቦት ፬ ቀን የተጻፈልን ደብዳቤ እንደደረሰን በዚህ ስብሰባ ጉዳይ እየተባበርን በጋራ እንድንራመድ ከተወሰነ በኋላ ተጋባዡን፥ የስብሰባውን ቀንና ቦታ፥ አጀንዳና የውክልናውን ልክ ተወስኖ በታሰበው ስብሰባ ላይ እንድንገኝ ጥሪ በመተላለፉ ኅብረቱ ቅሬታ የተሰማው መሆኑን ለጋባዡ ድርጅት በቃልም፥ ግንቦት ፫ ቀን በተጻፈ ደብዳቤም አሳውቀናል፡፡ ይኸ ዓይነት ስብሰባ በጋራ ስለሚጠራበት ሁኔታ ከኦነግ ጋር እየተመካከርን እያለንና በመኻላችን መሠረታዊ ስምምነት እንደነበረን ስናስታውስ የዚኸ ዓይነት አካሄድና አሠራር ችግር ያለው በመሆኑ በቀና መንፈስ የተጀመረውን ጥረት የሚያደናቅፍ ሆኖ ስላገኘነው አድራጎቱን በአግራሞት ተመልክተነዋል፡፡ ስለጉዳዩ ከኅብረቱ ተጠሪዎች ጋር በተደረገ የስልክ ውይይትና በተላከልንም ጽሁፍ መሠረት አካሄዱ እንዳልነውም እክል እንዳለበት የታመነበት መሆኑ ተጠቅሶልን ሆኖም ኅብረቱ ባቀረበው ሃሳብ መሠረት የተጠራ ስብሰባ እንደሆነ፥ ይኸም የመጀመሪያ ደረጃ (preliminary) ስብሰባ እንደሆነ፥ አጀንዳም እዚያው ስብሰባ ላይ የሚነደፍ እንደሆነ ስለተረጋገጠልን በአጠቃላይ ግን ምንም ችግር ቢኖር ኅብረቱ ምን ጊዜም የሚያስቀድመው የአገርንና የወገንን ጉዳይ ነውና፥ የተጠቀሱት እክሎች ቢከሰቱም በሕዝባችን ላይ ከተጋረጡት እጅግ ከባድ ችግሮች አንፃር በማየት የቀረበልንን ጥሪ ተቀብለን ተወካዮችን ልከናል፡፡ በተወካዮቻችንም አማካይነት በስብሰባው ላይ እንዲነሱ ያሰብናቸውንና የሕዝባችንን ትግል በአስተንማማኝ ሁኔታ እንዲቀጥል አስተዋጽዖ ይኖራቸዋል የምንላቸውን መሠረታዊ ነጥቦች ስብሰባው እንዲወያይባቸው በጽሑፍ አቅርበናል፡፡


ዋና መሥሪያ ቤት (Main Office)
ፖ.ሣ.ቁ./P.O.Box 73246
Washington, D.C. 20056-3246,U.S.A
ስልክ/Tel.: 202-291-4217;
ፋክስ/Fax: 202-291-7645

ኢትዮጵያ (Ethiopia)
ፖ.ሣ.ቁ./P.O.Box
Addis Abeba,Ethiopia
ስልክ/(Tel.) 251_______
ፋክስ/Fax:2511________

አውሮጳ (Europe)
Jonathan Str. 82
2524 JJ The Hague,
Netherlands
Tel/Fax 31 70 394 6132

በደብዳቤአችን ላይ እንደገለጽነውም በእኛ እምነት ዛሬ ሕዝባችን የተያያዘው ተጋድሎ እንዳለፉት ፋይዳቢስ የሽግግር ሂደቶች አንድ ድርጅት ወይም የተወሰኑ ድርጅቶች ስብስብ ሌላን የፖለቲካ ድርጅት ወይም ስብስብ የሚተኩበት ተራ የሥልጣን ዝውውር ወይም ቅብብሎሽ ተጋድሎ አይደለም። ትግላችን ከዚህ እጅግ የሰፋ ኅብረተሰባችን እንዳለ በፀረ-ዴሞክራሲና በአመፅ ከተገነባ የአገዛዝ ሥርዓት ወደ ሰላማዊ፥ ዴሞክራሲያዊና የተረጋጋ ኅብረተሰብ የሚሸጋገርበትን ሂደት ለማመቻቸት የሚደረግ ተጋድሎ ነው። ያለ ዴሞክራሲያዊ ሂደት ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መሸጋገር ይቻላል ማለት ዘበት ነውና ኢዴኃን ዴሞክራሲያዊው ሽግግር ዋና አራማጅ ኃይል በአጠቃላይ ኅብረተሰቡ መሆኑ ጽኑ እምነቱ ነውና የትግል ስትራቴጂውን ሁሉ ከዚህ አኳያ እየቀየሰ ከሕዝባችን ጎን ተሰልፎ ሲታገል ቆይቷል።

ከንጉሣዊ አገዛዝ ወደ ደርግ፥ ከደርግ አገዛዝ ወደ ኢሕአዴግ የተደረጉት ሽግግሮች ለሕዝባችን የኪሳራ ሂደቶች ሆነው ለመክሰም የበቁት በተለያዩ የታሪክ አጋጣሚዎች በምንመኘው መልክ ኅብረተሰባችን እራሱን በራሱ ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለማሸጋገር የሚያስችሉት ተቋሞችና እይታዎችም ሆኑ የፖለቲካና ሥነ-ልቡና ሁኔታዎች ተሟልተው ባለመገኘታቸው ነበር።

በኅብረታችን እምነት ለዚህ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ሽግግር መሳካት በሚደረገው ጥረት የፖለቲካ ድርጅቶች ብቻ ሳይሆኑ ትግላቸውን በቀጥታ ከፖለቲካ ጋር ሳያያይዙ ለአገርና ለወገን፥ ለመብት፥ ለሙያና ለሕጋዊ ጥቅም እንዲሁም ለባህላዊ ኅልውናና ለመሳሰሉት ዓላማዎች የሚንቀሳቀሱ ስብስቦች ሁሉ ሊካተቱበት ይገባል። እየደማና እየተዋከበም ቢሆን ከመንግሥት ቁጥጥር ውጭ ለመዳበር የሚሞክረው ነፃ ፕረስ ኅብረተሰባችንን ለዴሞክራሲያዊ ለውጥ ለማዘጋጀትና ለመቀስቀስ ባደረገው ጥረት አዳዲስና ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰቦች በአገራችን እንዲሰርፁ ተደርጓል። በነዚህና በመሳሰሉ ሌሎች በታሪካችን ያልነበሩ ክስተቶች ሳቢያ ቀደም ሲል የነበረው ክፍተት ዛሬ ተደፍኖ ኅብረተሰባችንን ለዴሞክራሲያዊ ሽግግር የሚወስድ ከመቸውም ይበልጥ የተመቻቸበት ሁኔታ ውስጥ እንገኛለን። በዚህም የተነሳ በታሪካችን ለመጀመሪያ ጊዜ ኅብረተሰባችን እንዴትና ወዴት ለመሄድ እንደሚፈልግ የሚያውቅ፥ በየደረጃው ከአብራኩ በፈለቁና በሚቆጣጠራቸው ተቋማትና ኃይሎች እራሱን በራሱ ወደ ተረጋጋ ዴሞክራሲያዊ ኅብረተሰብ ለማሸጋገር የሚችልበት የታሪክ ምዕራፍ ላይ ይገኛል የሚል ፅኑ እምነት አለን።

በኢዴኃን (በኅብረቱ) እምነት ዛሬ ዴሞክራሲያዊ የኢሕአዴግ ተቃዋሚ ኃይሎች ዋናና አንገብጋቢ ተግባር የኢሕአዴግ መሪዎች በዚህ መልክ ለማዝረክረክና ለማውደም የሚሞክሯቸውን እነዚህን የኅብረተሰባችን ድሎች መንከባከብና በነሱ ላይ እየገነቡ ወደፊት የመራመድ አደራ ነው። ከዚህ በመነሳት ዛሬ የግንቦት ድሎችም ሆነ በቀደሙት ዓመታት ሕዝባችን በትግሉ ቀስ በቀስ የገነባቸውን የደሞክራሲያዊ ሽግግር ዋስትናዎች መልሶ እጁ ውስጥ እንዲያገባ የሚካሄደው ትግል መሠረታዊ ዓላማ ለኛ በጣም ግልጽ ነው። በሕዝባዊ ትግል ኢሕአዴግን አስገድዶ የፖለቲካ ፓርቲዎችና የሲቪክ ስብስቦች ተወካዮች፥ የወጣቶችና የሴች፥ የሰራተኞችና የገበሬዎች፥ የሙያና የጥቅም፥ የባህል፥ የምሁራን፥ ወዘተ.. ማኅበራትና ስብስቦች ተወካዮች፥ የሐይማኖት መሪዎችና በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ስብስቦች፥ እንዲሁም የአገር ሽማግሌዎች የሚሳተፉበት ሰፊ አገር-አቀፍ ጉባዔ ተጠርቶ የዴሞክራሲውንና የሽግግሩን ሂደት መልክ የሚያስይዝበትን ሁኔታ ለማመቻቸት መሥራት ይኖርብናል። ወደዚህ ዓላማ ለመድረስ በሚደረገው ትግል የፖለቲካ ድርጅቶች ወሳኝ ሚና ቢኖራቸውም ይኸንን ተልዕኮና አደራ ለመወጣት የሚችሉት በሁለት ደረጃ በሚካሄዱ ትግሎች ይሆናል ብለን እናምናለን።

አንደኛው የኅብረተሰብ ክፍሎች ተወካዮች የተቻለውን ያህል የሚሳተፉበት ጉባዔ አዘጋጅቶ የጋራ ትግሉ መድረክ ከፖለቲካ ኃይሎች የሰፋ እንዲሆን መታገል ሲሆን፤

ሁለተኛው ሕዝባችንንና የተለያዩ የኅብረተሰቡ ክፍሎችን ይዘን በምናደርገው ትግል የኢሕአዴግ መሪዎች ተገደው ሰፊ አገር-አቀፍ ጉባዔ እንዲደረግ መታገል ይሆናል። ከዚህ ታሪካዊ ተልዕኮ አንፃር ሲታይ አሁን በኦነግ የተጠራው ስብሰባ የጋራ ትግላችን የመጀመሪያው ምዕራፍ እንደመሆኑ መጠን ዋና ተግባሩ ወደ አገር-አቀፉ ሰፊ ጉባዔ የሚመራን የጋራ ትግል ስትራቴጂ የሚነደፍበትን ሁኔታ ማመቻቸት ነው ብለን በማመን ይኸ ስብሰባ ይኸንን ታሪካዊ ሃላፊነት ይወጣ ዘንድ በቦታው በመገኘት የበኩላችንን ጥረት አድርገናል።

ምንም እንኳ በስብሰባው ላይ የገጠመን ወደ ስብሰባው እንድንመጣ ሲነገረን በጽሑፍም በቃልም ከተገለጸልን ውጭ ስብሰባው ቀደም ሲል በተዘጋጀ አጀንዳ ብቻ እንዲካሄድ የተደረገው ጥረት አግባብ ያለውና ጠቃሚ ሆኖ ባናገኘውም፥ ይኸ ክስተት የወደፊት የጋራ ሥራችን ላይ እንዳያጠላና ያልተጠበቀ መጥፎ ስሜትን እንዳያስከትል ባለን ቅን አስተሳሰብና በጎ ፍላጎት መሠረት ተወካዮቻችን ሃላፊነት በተሞላው መንፈስ መስተካከሎች እንዲደረጉ ሞክረዋል። የአገራችን ውስብስብ ችግሮች እንዲህ በአንድ ስብሰባም ይሁን በተወሰኑ ድርጅቶች ጥረት ብቻ የሚፈታ ባለመሆኑ በተወካዮቻችን አማካይነት በቃልና በጽሑፍ በዚህ ስብሰባ ውይይት ላይ እንዳቀረብነው ሁሉ ኅብረቱ ይኸ ስብሰባ የሚከተሉትን ውጤቶች ይዞ እንዲወጣ ያለንን ሃሳብ እንገልጻለን።

1ኛ) በዚህ ስብሰባ ላይ የተገኘን ድርጅቶች ትግላችንን ለማስተባበር አንድ የጋራ ስብስብ ለመፍጠር በመሠረተ ሃሳብ ደረጃ እንደተስማማን የጋራ መግለጫ እንዲሰጥ፤

2ኛ) ለቀጣዩ ጉባዔ ዝግጅት ከሁሉም ድርጅቶች የተውጣጣ የቀውጢ ጊዜ ግብረ-ኃይል እንዲሰየም፥ ለሚቋቋመው ግብረ-ኃይል በተለይም ስለ ትግል የጋራ ፕሮግራም፥ መዋቅር፥ ወዘተ... ስለሚዘጋጁ ሰነዶችና ሌሎች ተግባራት ዝርዝር መመሪያ ማውጣት፤

3ኛ) ከአንድ ወር እስከ ወር ተኩል ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ግብረ-ኃይሉ ሥራውን አጠናቆ አጠቃላይ ጉባዔ እንዲጠራና ስብስቡን (የጋራ ግንባሩን) መሥርቶ እንቅስቃሰውን በይፋ እንዲጀምር፤

ይኸ ስብሰባ በቀና መንፈስ እንደተዘጋጀ ማመን እንወዳለን። ስብሰባውን ያዘጋጁትንም ሆነ ከሩቅም ከቅርብም ተጉዘው በዚህ ስብሰባ ላይ የተገኙ ወገኖቻችንን በአገር ጉዳይ ለመወያየት ላደረጉት ጥረት እያመሰገንን፥ የሕዝብን ብሶት ሊያሳጥር የሚችል መልካም የተባበረ የትግል ጊዜና አይቀሬ የሕዝብ ድል እንዲበቁ ምኞታችንን እንገልጻለን።

የተባበረ የሕዝብ ትግል ያቸንፋል!!
ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!

---

ፋሲካ በለጠ
የኢዴኃኅ ሊቀ-መንበር